# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 243 ጥር 2 2005 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ እንዲሁም የኢትዮጲያ ወጣቶች ስብስብ የሆነው የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይልን ጨምሮ እየተናገሩት ያሉት፤ ነጻነትና ፍትህ፣ መልካም አስተዳደር፣ ሰርቶ ማደግ፣ እኩልነትና ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብትና ሌሎች፣ በዜግነት የሚገኙ መብቶች እንጅ አምባገነኖች የሚቸሩህ ችሮታዎች አይደሉምና ለቆምንለት አላማ በጋራ በጽናት በመታገል ለቀጣዩ ትውልድ መልካም አሻራን ለመጣል አሁን ተነሱ ነው ጥሪው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## በወያኔ ሰራዊት መካከል ቡሬ ግምባር ላይ ተፈጥሮ የነበረው የእርስ በርስ ውጊያ ዘርን መሰረት ያደረገ እንደነበር ታወቀ

በቅርቡ በተገባደደዉ የፈረንጆቹ አመት ማለቂያ አካባቢ በቡሬ ግንባር ልዩ ስሙ ማገንዳ አየተባለ በሚጠራው ቦታ ላይ የሰፈረዉ የኢትዮጲያ መከላከያ ስራዊት ጎራ ለይቶ እርስ በርሱ የተላለቀዉ ትግርኛ ተናጋሪ በሆነዉ ጦርና በተቀሩት ኢትዮጵያዉያን መካከል በተፈጠረዉ አለመግባባት መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ወታደራዊ ደህንነት ቃል አቀባዮች ታማኝ የሆኑ የመከላከያ ምንጮችን ጠቅሰዉ በላኩልን ዜና ገለጹ። በየትኛዉም ቦታ በሰፈረዉ የኢትዮጵያ ሰራዊት ዉስጥ “የበላይ ነን” በሚሉ ትግርኛ ተናጋሪዎችና በተቀረዉ የሰራዊቱ አባላት መካከል ምን ግዜም ቢሆን ዉጥረትና ትናንሽ ግጭቶች የሚከሰቱ ሲሆን የቡሬዉን ግጭት ልዩ የሚያደርገዉ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸዉና መሳሪያ የታጠቁ የሰራዊቱ አባላት ለትግራይ መኮንኖች አንታዘዝም ወይም የትግራይ አዛዦች አያዝዙንም ብለዉ በፈጠሩት ግጭት ቁጥራቸዉ ከአንድ መቶ በላይ የሚሆኑ ወታደሮች ላይ የሞትና የአካለ ጉዳት በመድረሱ ነዉ።

በቡሬ ግንባር የተፈጠረዉ የእርስ በርስ ወታደራዊ ግጭት ዜና በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች እንዳይሰማ የወያንኔ አገዛዝ ከፍተኛ ጥንቃቀ ቢያደርግም የኢትዮጵያ ሳተላይት ተ|ቪዥንና ሬድዮ አገልግሎቶች ግጭቱ በተፈጠረ በደቂቃዎች ዉስጥ ዘናውን በመላዉ አለም ማሰራጨት እንደቻለ ለማወቅ ተችሎአል። ስለሆነም ዛሬ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በብዛት በሰፈረባቸዉ የአገሪቱ አካባቢዎች ሁሉ ሰራዊቱ በትግርኛ ተናጋሪዎችና ለትግራይ ወታደራዊ አዥገሮች አንታዘዝም በሚሉ ሁለት ትላልቅ ጎራዎች ተከፍሎ ከፍተኛ ፍጥጫ ዉስጥ በመግባቱ የወያኔው አገዛዝ ክፉኛ እንደተደናገጠ ከየቦታዉ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዘ በቡሬ ግንባር ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ ወታደሮች ያሰር ሲሆን ለግምገማ ትፈለጋላችሁ በሚል ሰበብ አራት ሻለቃ ጦር ትጥቅ አስፈትቶ ወታደሩን እያንገላታ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል። ከአንድ ሳምንት በላይ የፈጀዉና አሰልቺዉ የወያኔ ግምገማ የተገባደደ ቢሆንም በቡሬ ግንባር ከሚገኘዉ የመከላከያ ሰራዊት ዉስጥ አራት ሻለቃ ጦር አሁንም ትጥቁን ፈትቶ በወያኔ ካድረዎች አጥንት የሚስብር ዘለፋና ዛቻ እየደረሰበት መሆኑን ለግንቦት ሰባተ ድምጽ ዝግጅት ክፍል ስልክ እየደወሉ የተናገሩ የሰራዊቱ አባላት ገልጸዋል። ይህ የሰራዊቱ አባላት ከግንቦት ሰባት ጋር የሚያደርጉት የስልክ ግንኙነት ያበሳጨዉ ወያነ በቡሬና በአካባቢዉ የስልክ ግንኙነት እንዲቋረጥ ማድረጉ የሚታወስ ነዉ። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በጭፍን የወያኔ ደጋፊነት በመሰለፍ በህዝብ ልጆች ላይ ለሚፈጸሙ ጥቃቶች ተባባሪ የሆኑ ወገኖች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ( ኦነግ ) ጠየቀ

የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ዓላማ በመንግስት ስርዓት ላይ ያነጣጠረ እንጂ በማናቸውም ብሄሮችና ብሄረሰቦች ላይ የጥላቻ ወይም የበቀል ስሜት ያዘለ ትግል አለመሆኑን በመገንዘብ በጭፍን የወያኔ ደጋፊነት በመሰለፍ በህዝብ ልጆች ላይ ለሚፈጸሙ ጥቃቶች ተባባሪ የሆኑ ወገኖች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ጠየቀ።

ኦነግ "የኦሮሞ ህዝብ ትግልን አላማ ለማስቀልበስ በወያኔ የሚፈጸም ወደርየለሽ ወንጀል" በሚል ባወጣው መግለጫ የትግሉ ዋነኛ ዓላማ የኦሮሞ ህዝብ የሃገር ባለቤትነት መብቱን እንዲጎናጸፍ ማስቻል ነው።እናም ይህን ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ በጨቋኙ የወያኔ መንግስት ላይ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም ብሄር ወይም ህዝብ ላይ አያነጣጥርም- ነው ያለው።

በማያያዝም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሚማሩ የኦሮሞ ብሄር ተወላጅ ተማሪዎች ላይ በወያኔ አገዛዝ የሚፈጸመውን የተቀነባበረ ጥቃት አውግዞ ወያኔ የኦሮሞ ህዝብ ትግል በሌሎች ዘንድ እዲወገዝና በጥርጣሬ ዓይን እዲታይ የተለየዩ ሴራዎ ችን ሲሸርብ ኖሯል ፤ ኦሮሞን ከተለያዩ ህዝቦችና ብሄረሰቦች ጋር በማጋጨት ደም አቃብቷል፤ ባለፉት አስር ዓመታት ደግሞ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ወያኔ የሰዉ መግደል ወንጀል ሙያዉን ይዞ አሜሪካ መጣ-ጋዜጠኛ አበበ ገላዉን ለመግደል ያደረገዉን ሙከራ “ኤፍ ቢ አይ” አከሸፈ

ኤፍ ቢ አይ በሚል ምህጻረ ቃል የሚታወቀዉ የአሜሪካ የፌዴራል ወንጀል ምርመራ ግበረሃል የዘረኛዉ ወያኔ አገዛዝ ነብሰ ገዳይ ግብረ ሀይል የማሳቹሰትስ ግዛት ዋና ከተማ በሆነችዉ ቦስተን ዉስጥ ጋዜጠኛ አበበ ገላዉን ለመግድል ሲያሴሩ የነበሩ ወንጀለኞችን በቁጥጥር ስር አዉሎ ምርመራ መጀመሩን የኢትዮጵያ ሳተለይት ቴሌቪዥን ዘገበ። ይህ የወያኔ ተላላኪ የሆነዉ ወንጀል ፈጻሚ ቡድን ጋዜጠኛ አበበ ገላዉን ለመግደል ሙከራ ያደረገዉ ታዋቂዉ ጋዜጠኛ አበበ ገላዉ ባለፈው ወር መባቻ ላይ ለኢሳት ገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ወደ ቦስተን በተጓዘበት ወቅት አንደነበር ከኢሳት ዘገባ መረዳት ተችሏል። ከዚሁ ከኢሳት ዘገባ መረዳት እንደተቻለዉ የወያኔ አገዛዝ ከአዲስ አበባ የሰጠዉን የግድያ የቤት ስራ ለመስራት በመዶለትና ግብረአበሮቹን በማስተባበር ላይ እንዳለ እጅ ከፍንጅ የተያዘዉ ግኡሽ አበራ በሚል መጠሪያ ስም የሚታወቀዉና የህወሃት ሰላይ መሆኑ የሚነገርለት ግለሰብ አንደሆን ለማወቅ ተችሏል።

በአሜሪካ ሀገር የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቆ የሚኖረውና እራሱን ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ (ህወሃት) ብሎ የሚጠራው ጽንፈኛ የዘር ድርጅት አባልና ሰላይ የሆነዉ ግኡሽ አበራ አበበ ገላዉን ለመግደል በማሴር ሶስት የወንጀሉ ተባባሪ የሚሆኑ ግለሰቦችን መልምሎ ድርጊቱን ለመፈጸም የመጨረሻ መሰናዶ ካደረገ በሁዋላ የግለሰቡን እንቅስቃሴ በቅርብ ይከታተሉ የነበሩ የኤፍ ቢ አይ መሪማሪዎች ሴራውን በግዜ ማከሸፋቸው ተረጋግጧል።

ቦስተን ዉስጥ የሚገኙ የኤፍ ቢ አይ ወንጀል መርማሪ ቡድን አባላት ግኡሽ አበራ ወንጀሉን ለመፈጸም በዝግጅት ላይ በነበረበት ወቅት ከግብራበሮቹ ጋር የተለዋወጣቸውን መልእክቶች በመጥለፍ በእሱና አብረው በሚኖሩ ሌሎች አራት ግለሰቦች ላይ ክትትልና ምረመራ ማድረግ በመጀመራቸዉ ወንጀለኞቹ አበበ ገላዉ ላይ ምንም ጉዳት ከማድረሳቸዉ በፊት ከቁጥጥር ስር ማድረግ ችለዋል። ከኤፍ ቢ አይ በተገኘዉ መረጃ መሠረት ግኡሽ አበራ ከወንጀል ጓደኞቹ ጋር የተለዋወጣቸው መልእክቶች ጋዜጠኛ አበበ ገላው ወደቦስተን የመሄዱን አጋጣሚ በመጠቀም በመሳሪያ ተኩሶ የመግደል እቅድ አንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

የቦስተን ቅርንጫፍ ኤፍ ቢ አይ ቃል አቀባይ እና ልዩ መርማሪ የሆኑት ሚስተር ግሬግ ኮምኮዊች ምርመራው አሁንም (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ለአማራው መብት የሚታገል ሲቪክ ተቋም ተመሰረተ

ባለፉት 21 አመታት በአማራው ብሄረሰብ ላይ በገዥው ፓርቲ የደረሰበትን መፈናቀል፣ መገፋት መገለልና የዘር ማጽዳት እርምጃ ለመታደግና ለመታገል ያለመ ሲቪክ ድርጅት ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ተመሰረተ።

ሞረሽ ወገኔ የአማራው ድርጅት የተሰኘው ይህ ሲቪክ ተቆም ከሁለት ቀናት በፊት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላለፉት 21 አመታት የአማራው ብሄረሰብ አባል ተዋራጅና ተሸማቃቂ ተደርጎል፣የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅሞቹ ተነጥቀዋል ከምስራቅ፣ከደቡብ ምእራብ፣ከደቡብና ከመሀል ኢትዮጵያ መኖር አትችልም ተብሎ ሀብት ንብረቱ ተነጥቆ ተባሮል ሲል ገለጧል።

ላለፉት 21 አመታት በገዥው ፓርቲ በአማራው ህብረተሰብ ላይ እየተፈጸመ ያለው የዘር ማጽዳት ዘመቻ ሊገታ ይገባዋል ያሉት የሞረሽ ወገኔ ሊቀመንበር አቶ ተክሌ የሻው ይህን ለማድረግ መደራጀት ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ሆኖብናል ብሉዋል።

ግባችን የአማራው ህልውና እንዲጠበቅና በመላው ሀገሪቱ የመስራትና የመኖር መብቱ እንዲከበር ነው ያለው የሞረሽ ወገኔ የአማራው ድርጅት ጋዜጣዊ መግለጫ ይህን ሲያደርግ የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ የአንድ ብሄረሰብን የማግነን፣ የከፋፍለህ ግዛ መርህንና ዘረኝነትን አጥብቆ በመታገል እንደሆነ ገልጧል።

አማራው ሲደራጅ አምርሮ የሚታገለው ግፍ ያደረሰበትን የገዥው ፓርቲን ስርአትና የቀረጸውን ፖሊሲ ነው ያለው የሞረሽ ሊቀመንበር አቶ ተክሌ የሻው ማህበረሰባችንን የማዳን እንጂ ሌላውን የማጥቃት አላማ የለንም ብሉዋል።

የድርጅቱ መስራቾችና አባላት አማራው ከሚደርስበት ግፍና በደል ለማውጣትና በሺዎች ለሚቆጠሩ ለተፈናቀሉ ወገኖቹን ለመታደግ እውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውንና ሀሳባቸውን አስተባብረው ለመስራት መቁረጣቸውን ባወጡት የአቆም መግለጫ አስታውቀዋል።

## ፅናት እንደ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች

እንደገና ጩኸት፣ አንደገና ዋይታ እንደገና ግድያ በሀረር ከተማ! ባለፈዉ ሳምንት ሙስሊም ወገኖቻችን በሰላማዊ ተቃዉሞ ያቀረቡትን መበታችን ይከበር የሚል ጥያቄ ወያኔ አንደለመደዉ ነብስ ያላወቀ የሰባት አመት ልጅ በመግደል አረመኔያዊ መልስ ሰጥቷል። ተቃውሞ ጋር በተያያዘ ታዳጊ ህጻን ላይመለስ በወያኔ ጥይት ተገድሏል፤ ረጅሙ ተስፋ ከዚህበፊት እንደተጨፈጨፉት ለጋ ህጻናት በወያኔ ጥይት ህይወቱ በአጭር ሊገታ ግድ ሆኗል።

የእስልምና እምነት ተከታይ ወንድሞቻችን “በእምነታችን ላይ የዘረኛው ወያኔ የደም እጅ ጣልቃ ገብነት በአስቸኳይ ይቁም! የሃይማኖት ነጻነት ይከበር! “ሲሉ እያሰሙ ያሉት ተቃውሞ 365 ቀናትን በማስቆጠር በመላው ሀገሪቱ ተስፋፍቶ በሀረር የ7 አመት ህጻን ልጅና ወላጅ እናቱ የጨካኙ ወያኔ የጥይት ሰለባ በመሆን ወያኔ መንበረ ስልጣኑን እንደያዘ ለመቀጠል የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ እየሞተ ነጻነቱን ለማስከበር የሚደረገው ግብግብ ቀጥሏል።

በአወልያ የተጀመረውና ዛሬ ወደ ሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የተዛመተውና አሁን ወደክርስትና እምነት ተከታዮችምም እያጠቃለለ ያለው የድምጻችን ይሰማ አመራሮች ጥያቄ ዛሬም ለነጻነታችን እንታገላለን እየሞትን እንወለዳለን፤ ወያኔ ለነጻነት ለጥያቄያችን የጥይትምላሽ እየሰጠ ወገኖቻችንን እየጨፈጨፈ ቢሆንም ለቀቆምንለት አላማ፤ ለእምነታችን ነጻነትና፣ ለማንነታችን ባይተዋር ሳንሆን ትግላችን ድል እስከተገኘ ድረስ ይቀጥላል ሲሉ ለወያኔ በድጋሜ ማስጠንቀቂያ አስተላልፈዋል።

ይሁን እንጅ ቅንጣት ያህል ለዜጎች መብት መከበር ደንታ የሌለው ወያኔ ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ህይወት በመቅጠፍ፣ ርህራሄ የሌለው ግፈኛ መሆኑንና በስልጣኑ የሚመጣበትን ለመመከት ማናቸውንም ወንጀሎች ከመፈጸም እንደማይመለስ ለማሳየት የአርፋችሁ ተቀመጡ መቀጣጫ ይሆን ዘንድ ህጻናትን በመግደል የአውሬነት ባህሪውን ቀጥሎበታል።

ዛሬ በመላው አለም የዜጎች መብት ተብለው የተደነገጉት የንግግር፣ የመሰብሰብ፣ የመጻፍ፣ የመጠየቅ፣ የመምረጥና የመመረጥ ነፃነቶች በእኛ ሀገር ወይም በወያኔ መንደር እነዚህን መብቶች መጠየቅ የሽብርተኛ ታርጋ የሚያስለጥፍና የበርካታ ንጹሃን ዜጎችን ህይወት የሚያስቀጥፍ መሆኑ እየታየ ነው።

የእስልምና እምነት ተከታይ ወገኖቻችን ላለፉት 365 ቀናት ለነጻነት ባላቸው ቆራጥነት፣ ፅናትና ፍቅር የተነሱለትን አላማ ከግብ ለማድረስ የትግል ስልታቸው አይሎ ከፍርሃት አረንቋ በመውጣት የሃይማኖት ነጻነት ይከበር ዘንድ በአንድ ድምጽ ትግላቸውን ቀጥለዋል፤ ይህም ለበርካታ ኢትዮጵያውያን ትልቅ ትምህርት እየሰጠ በየአቅጣጫው የመብታችን ይከበር ጩኸቶች እየተነሱና እተፋፋሙ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የሙስሊሙ ህብረተሰበ ጥያቄ የመብትና የነጻነት ጥያቄ መሆኑን ተረድቶ ትግሉን በመቀላቀል የአገሩን አንድነትና የራሱን መብትና ነጻነት እንዲያስከብር ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አገራዊ ጥሪ ያደርጋል።

የዜጎችን የነጻነት ጥያቄ በወያኔ የጥይት አፈ ሙዝ ከቶ ማፈን እንደማይቻል የተረዱት ወያኔዎች፤ የእርስ በርስ ብጥብጥ ለማስነሳት ሙከራዎችን ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት ራሱ ወያኔ እንጅ ሌላ አለመሆኑን ተረድቶ ህዝቡ ከዚህ የህወሃት መሰሪ እቅድ መጠንቀቅ ይኖርበታል።

ህዝቡ ነፃነቱን ለመከላከል አቅም የሚሰጡትን የራሱን ነጻ ማህበራዊ የእምነት ተቋማትን የሚያጠናክርበትን ግንባታ በንቃት መስራት ያስፈልገዋል። በተለይም አሁን በኦርቶዶክስ እምነት እየተስተዋለ ያለውን የወያኔን ጣልቃ ገብነት ለመታገል ህዝበ ምእመናኑ በአንድ ድምጽ የሃይማኖታችን ነጻነት ይከበር ዘንድ እንደሙስሊሙ ወገናችን እጅ ለእጅ ተያይዞ በሀገራችን ሰላም፣ እኩልነት፣ ፍትህ፣ ነጻነት እና አንድነት እንዲኖር በጽናት መታገል ያስፈልገዋል።

መደገገፍና ሰበአዊነት ከባህላችን የወረስናቸው ሲሆኑ፣ ለቆምንለት አላማና ለሃገራችን፣ ለነጻነታችን፣ ለአንድነታችን በእምቢተኝነት የምንታወቅ እኛ ኢትዮጵያውያን አሁንም ለወያኔ በየቦታው ጣልቃ ገብነትና ከፋፍለህ ግዛ ድርጊት በዝምታ እጃችንን አጣጥፈን ልንመለከተው አይገባም።

የሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ እንዲሁም የኢትዮጲያ ወጣቶች ስብስብ የሆነው የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይልን ጨምሮ እየተናገሩት ያሉት፤ ነጻነትና ፍትህ፣ መልካም አስተዳደር፣ ሰርቶ ማደግ፣ እኩልነትና ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብትና ሌሎች፣ በዜግነት የሚገኙ መብቶች እንጅ አምባገነኖች የሚቸሩህ ችሮታዎች አይደሉምና ለቆምንለት አላማ በጋራ በጽናት በመታገል ለቀጣዩ ትውልድ መልካም አሻራን ለመጣል አሁን ተነሱ ነው ጥሪው።

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና ዴሞክራሲ ንቅናቄ ህዝባችን እንደሙስሊሙ ወገኑ በጽናት እየታገለ የሚያስፈልገውን መሰዋእት በመክፈል የህዝብ፣ የሀገር እድገትንና ደህንነትን አንቀው የያዙ ዘረኞችን በማስገደድ አሊያም በማስወገድ ለሀገራችን ነጻነትና የዴሞክራሲያዊ ባህል ግንባታ ፈር ቀዳጆች እንሁን ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ወጣቱ ፖለቲከኛ አንዱለም አራጌ ህገ-መንግስታዊ መብቴ ተጥሶ ዘመድ አዝማድ እንዳይጠይቀኝ ተደረኩ ሲል ወያኔን ኮነነ

በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ የፈጠራ ክስ ተመስርቶበት የግፈኞች የዕድሜ ልክ እስራት ሰለባ የሆነዉ ወጣቱ የፖለቲካ ድርጅት መሪ አንዱአለም አራጌ የወያኔ አገዛዝ ከሌሎች አስረኞች ለይቶ እኔን ብቻ ዘመድ አዝማድ እንዳይጠይቀኝ አድርጓል ሲል ማማረሩ ተሰማ። አንዷለም አራጌ ይህንን ወያኔ የዕድሜ ልክ እስራት ከፈረደበት በሁዋላም የሚፈጽምበትን በደል በምሬት የተናገረዉ የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ እንዲጠይቁት የተፈቀደላቸው ጓደኞቹ የአንድነት ፓርቲ አመራሮች በቃሊቲ ተገኝተው በጎበኙት ጊዜ ነው።

የትግል ጓደኛቸዉን ለመጠየቅ በዕለተ ገና ቃሊቲ እስር ቤት የሄዱት ከአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች መካከል ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ፣ አቶ ተመስጌን ዘውዴ፣ አቶ ዘካርያስ የማነብርሃን፣ አቶ ዳንኤል ተፈራና አቶ ሙላት ጣሰው ሲሆኑ ከእነሱ በተጨማሪ ሌሎች ከአስር በላይ የሚሆኑ የፓርቲዉ አባላትም የአንዱአለም የጤና ሁኔታና የእስር ቤት አያያዝ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ቃሊቲ መሄዳቸዉ ታዉቃል።

ከኔ የእስር ቤት መከራ ይልቅ በጣም የሚያሳስበኝ የገዥው ፓርቲ አፈናና ጭቆና እንዲሁም በዚህ ሁኔታ ዉስጥ የሚታገሉ ባልደረቦቹ ጉዳይ ነዉ ያለዉ አንዱ አለም አራጌ ወያኔ እሱ ላይ ያደረሰዉ አይነት በደልና መከራ በትግሉ ጎራ ዉስጥ በሚገኙት ጓደኞቹ ላይ እስካሁን ድረስ ባለማድረሱ የህሊና ሰላም እንደሚሰማው ተናግሯል፡፡ ወጣቱ ፖለቲከኛ በዚሁ ጊዜ ቃሊቲ ለተገኙት የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት”በፍቅርና በመተሳሰብ የምንኖርባት ኢትዮጵያ ትናፍቀኛለች”በማለት ህያው ራዕዩንና ውስጣዊ ምኞቱን ገልጾላቸዋል። በመጨረሻም “ለእኛ ቀርቶብን ለልጆቻችን እንኳን የተሻለ ማረሚያ ቤት ማስተላለፍ አለብን” ብሎ ሲናገር የሰሙት የማረሚያ ቤቱ ኃላፊ ብስጭት የተቀላቀለዉ የዘለፉ ቃል በመሰንዘር ወደ ታሰረበት ክፍል እንዲመለስ ተደርጎ የእለቱ ጉብኝት ተፈጽሟል።

## የወያኔ አገዛዝ ሰራዊት አባላት ከ150 ያላነሱ የሱሪ ብሄረሰብ አባላትን በአሰቃቂ ሁኔታ መግደላቸው ተጋለጠ

በአንድ የሰብአዊ መብት ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ የውጭ አገር ዜጋ በሱሪ አካባቢ ተገኝቶ ያየውን ሁኔታ አጋልጧል። ይህ የውጭ ሃገር ዜጋ እንደገለጠው ዲሰምበር 20፣ 2012 የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በባሌሳ ሱሪ መንደር፣ ቢያሆላ ወይም በአገሬው ቋንቋ ነጭ ድንጋይ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ መጡና ነዋሪዎችን ከበቡዋቸው ብሏል። በመቀጠልም ወታደሮቹ ወንዶችን፣ ሴቶችንና ህጻናትን እርስ በርስ ካሰሩ በሁዋላ ወደ ዲዲቢ ጫካ ወሰዱዋቸው። 7 ወጣቶች ብቻ ሲያመልጡ ሁሉንም በአንድ ጊዜ ረሸኑዋቸው። በመንደሩዋ 154 ሱሪዎች ይኖሩ ነበር በማለት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እያደረሰ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ይፋ አድርጓል።

ይሄው ዜጋ ንዳረጋገጠው የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ይህ እልቂት እንዳይነገርባቸው የሚችሉትን ሁሉ እየጣሩ ነው። ነገር ግን እግዚአብሄር ይመስገን ዜናው ይፋ ወጣ። ይህ በደቡብ ኢትዮጵያ እየተካሄ ያለ የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው። የአሜሪካና የእንግሊዝ መንግስታት ለምን ይሆን የኢትዮጵያን መንግስት የሚደግፉት? አሸባሪነትን መደገፍ ሳይሆን መዋጋት አልነበረባቸውም? በማለት የተመለከተውን ዘግናኝ ጭፍጨፋ ለዓለም ይፋ አድርጓል።

በመቀጠልም የሟቾቹ አስከሬን በዲቢዲብ ጫካ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ እንዲቀበር ተደርጓል። አንዳንድ አስከሬኖች በጥንብ አንሳ አሞሮች እና በአውሬዎች ተበልተዋል። አብዛኞቹ ህጻናት በአቆቦ ወንዝ ላይ ተጥለዋል። ከጭፍጨፋው በሁዋላ ወታደሮች ይህን ድርጊት ሪፖርት ባደረገው ላይ ሁሉ ከዚህ የበለጠ አስከፊ እርምጃ እንደሚወስዱ አስጠንቅቀዋል ብሏል። በመጨረሻም በሱሪዎች ላይ የሚፈጸመው ግድያ እንደቀጠለ ነው። በየወሩም እየከፋ በመሄድ ላይ ነው። ማንም ግን ስለችግሩ የተናገረ አካል የለም። በምእራብ አገሮች በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ሲገደሉ የምእራብ ሚዲያዎች ሰፊ የዜና ሽፋን እንደማይሰጡት ሁሉ ፣ በደቡብ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በዚህ መጠን ሲገደሉ ግን የዜና ሽፋን ሊያገኙ አልቻሉም ብሏል።

ባለፉት ሳምንታት ብቻ 147፣ ከሶስት ወራት በፊት 30፣ ከአራት ወራት በፊት ደግሞ 70 ሰዎች መገደላቸው በስፋት መዘገቡ ይታወሳል።

## ፍሬ አልባ በለሶች!!!

አገራችን ኢትዮጵያ ብዙ የጥበብ ሰዎችን አፍርታለች። ሀዲስ ዓለመየሁን፤ በዓሉ ግርማን፤ ብርሃኑ ዘሪሁንን፤ አቤ ጉበኛውን፤ ሎሬት ፀጋየ ገ/መድህንን፤ ጥላሁን ገሰሰን አንረሳቸውም። እነዚህ የጥበብ ሰዎች የህዝባቸውን ልቅሶ ያለቀሱ፤ ሃዘኑን ያዘኑ፤ብሶቱን ከፍ ባለ ድምጽ የተናገሩለት እና እውነትን የፈለጉ ስመ ጥር ባለሙያዎች ነበሩ። እነዚህ ባለሙያዎች እንደ እሥሥት ራሳቸውን ሳይቀያይሩ ለሂሊናቸው ታምነው፤ በጥበባቸው ስለ እውነት ሰብከው ያለፉ ስም ጥር ባለሙያዎች በመሆናቸው ተረስተው የሚቀሩ አይደሉም።

ዛሬም የእነዚህን ስም ጥር ባለሙያዎችን መስመር የሚከተሉ አሉ። ህዝብ ሲያለቅስ አብረው የሚያለቅሱ፤ የህዝቡን ብሶት የሚናገሩለት፤ ከሂሊናቸውና ከእውነት ጋር መቆምን የመረጡ ብርቅየ የጥበብ ሰዎች አሉ። ሥራቸው በሮሮ ውስጥ ላለ ህዝብ ተስፋ፤ አቅም የለኝም ለሚለው ብርታት የሚሆን እንደ ቤተ መቅደስ እጣን መዓዛው ያመረና የተወደደ ነው። እነዚህ የጥበብ ሰዎች የህፃን ነብዩን እንባ አይተው ዝም ማለትን ያልመረጡ፤ ሰው በዘሩ ብቻ ተመርጦ ሲዋረድ፤ በዘሩ ብቻ ተመርጦ ሲሾም እያዩ ምን አገባኝ ያላሉ፤ አገሪቷን አገር ሊያሰኙ የሚችሉ ወግና ልማዶችን ከሚያጠፉ ቡድኖች ጎን መቆምን የተጠየፉ፤ ጥቂቶቹ ብዙሃኑን ተጭነው፤ ብዙሃኑም ጥቂቶቹን ተሸክመው ስቃያቸው በዝቶ ሲኖሩ አይተው እንዳላዩ መሆንን እንደ ውረደት የቆጠሩ፤ ብኩርናቸውን ለምናምንቴ ነገር ሲሉ አሳልፈው ያልሰጡ ብርቅየ ልጆች አሁንም ኢትዮጵያ አሏትና ደስ ይለናል።

የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንደሚባለው ሆነና ብኩርናቸውን በምናምንቴ ነገር ለውጠው ከህብረተሰቡ ተነጥለው ብቻቸውን በበርሃ የቆመን ፍሬ አልባ በለስ የሚመስሉ ደግሞ አሉ። እነዚህ ራሳቸውን ከጥበብ ሰዎች ተርታ ለማቆም ቢውተረተሩም እንደ ፍሬ አልባዋ በለስ ባዶ በመሆናቸው ለትውልዱ የሚተውለት መልካም አሻራ ከእነዚህ ዘንድ አልተገኘም። ግዜ ካነሳው ጋር እየተነሱ፤ ግዜ የጣለውን ደግሞ እየረገጡ ራሳቸውን እንደ እሥሥት እየቀያየሩ የሚገለጡ አርቲስት ተብየዎች በነሎሬት ፀጋየ ገ/መድህን፤ በነበዓሉ ግርማ፤ በእነ አዲስ ዓለማየሁ፤ በእነ ብርሃኑ ዘሪሁን፤ በእነ አቤ ጉበኛ አገር መፈጠራቸው በእጅጉ ይገርማል።

ጥበብ እውነት ነች። የጥበብ ሰው መሆን ማለትም የእውነት ሰው ማለት ነው።የጥበብ ሰው ከሌላው ተራ ህዝብ የተለየ ነው። የጥበብ ሰው ክብሩና ሞገሱ ለእውነት መቆምና እውነትን መፈለግ እንጂ እንድ ዔሳው ብኩርናውን ዛሬ ተብልቶ ነገ ለሚረሳ ምስር ወጥ የሚቀይር ማለት አይደለም። የጥበብ ሰው ህይወቱ እውነትን መፈለግ እና ለእውነት ዘብ መቆም ነው። ያ እርሱ ፈልጎ የገኘውን እውነት፤ ያ እርሱ ዘብ የሚቆምለትን እውነት በልዩ ተሰጥኦው ለህዝቡ ማስተማርና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ መጣር ደግሞ መጨረሻው የህይወት ግቡ ነው። እውነትን ያልፈለገ እና እውነትን በህረተሰቡ ውስጥ ማስረፅ የተሳነው የጥበብ ሰው እንደ ሌለ ራሱን ቢቆጥር ይሻለዋል። የጥበብ ሰው የህብረተሰቡ ፋና ወጊና አስተማሪ ነው ተብሎ ሊወደድ የሚችለው ለእውነት ዘብ ለመቆም ወኔው ያለው በመሆኑ ነው። ለእውነት ዘብ መቆምን የመረጠ ግዜ በህብረተሰቡ ፊት ሞገስና ክብርን ያገኛል፤ ሲያልፍም ስሙ በደጉ እየተነሳ ይኖራል እንጂ ተረስቶ አይቀርም።

ከዥንጉርጉሩ የእናት ሆድ የተወለዱ ሌሎች “የጥበብ ሰው” ነን የሚሉ ብዙ ናቸው።ከጥበብ ጋር ግን ራሳቸውን ለማዋሃድ ወኔውን ማጣችውን ባየን ግዜ በእጅጉ እናፍራላቸዋለን። እነዚህ በኢቲቪ መስኮት ብቅ ብለው በህፃን ነብዩ ደምና አጥንት ላይ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተነባብሮና ረዝሞ የተሠራውን ህንፃ ብቻ ተመልክተው፤ ያን ህያው ብላቴና ረስተው ግዑዙን ህንፃ ብቻ የሚያደንቁትን አርቲስት ተብየዎችን ማየት በእውነት አሳፋሪ ነው። የጥበብ ሰው ከግዑዝ ይልቅ ህይወት ላለው ህያው ነገር ይራራል፤ህመሙ ያመዋል፤ ራቡ ይርበዋል፤ ስቃዩ ያሰቃየዋል እንጂ የድንጋይ ቤት ርዝመት አያስደምመውም። ከጥበብ ጋር ያልተዋሃደ እና ብኩርናውን ለምናምንቴ ነገር አሳልፎ የሰጠ ግን እንዲህ ነው። ከህያው ነገር ይልቅ ህይወት የሌለው የማይናገር፤ የማይስቅ፤ የማይሰማ ግዑዝ ነገር ልቆ ይታየዋል።

ከሰሞኑ ደግሞ አርቲስቶች የተባሉት ተሳብሰበው የህወሃትን ጦር ሰፈር ጎበኘን ማለታቸውን ሰምተናል። ይሄ ምንም ችግር ያለው ነገር አይደለም። የጎበኙት የጦር ሰፈር ግን ለኢትዮጵያ ክብርና አንድነት የሚሰራ ሳይሆን አገሪቷን በዘርና በቋንቋ ከፋፍሎ እንዲያውም “አማራና ተፈጥሮ የትግራይ ቀንደኛ ጠላቶች ናቸው” ብሎ በሁለቱ ህዝቦች መካከል ጠላትነትን ለመተክል ሌተ ተቀን በሚሰሩ ቡድኖች የሚመራ መሆኑን ለማስታወስ ግዜው አሁን ነው። ይሄን የጦር ሰፈር የሚመሩት በአንዲት ጀንምበር በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ወደ ሁለት መቶ የሚሆኑ ንፁሃን ዜጎችን የገደሉ ናቸው። ይሄን የጦር ሰፈር የሚመሩ ቡድኖች በጋምቤላ እና በዖጋዴን ህዝቦች ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈፀሙ ናቸው። ይሄን የጦር ሰፈር የሚመሩ ሰዎች የዜጎችን የእምነት ነፃነት በመጋፋት እኛ የመርጥነውን አምላክ አምልክ እምቢ ካልክ ግን አሸባሪ ነህ ብለው ንጹሃን ዜጎችን የሚያሸብሩ ቡድኖች ናቸው። ይሄን የጦር ሰፈር የሚመሩት ቡድኖች እጅግ ኋላ ቀር ዘረኞች፤ ከመንደራቸው ዘልቀው ሂደው ማሰብ የማይችሉ መንደረተኞች ናቸው። ይሄን የጦር ሠፈር የሚመሩ ቡድኖች ህዝቡ አማራጭ የመረጃ ምንጭ እንዳይኖረው መገናኛ ብዙሃንን አፍነው፤ ጋዜጠኞችን አስረው፤ ገድለው፤ ከአገር አሳደው፤ ዜጎች በነፃነት እንዳይፅፉ፤ በነፃነት እንዳያስቡ፤ በነፃነት እንዳይናገሩ ያደርጉ ናቸው።

በእነዚህ ቡድኖች ለጉብኝት የተጋበዙ አርቲስቶች ብረቱን ብቻ ሳይሆን ከብረቱ ጀርባ ያለውንም እውነት ለማየት የሚያስችል ማስተዋል አይኖራቸውም ብለን ተስፋ አንቆርጥም። ዛሬ ህወሃቶች ገንብተነዋል የሚሉትን ብረት ለምንና እንዴት ሲጠቀሙት እንደቆዩም ዘር ብለው መርምረው እውነቱን ለማግኘት ብቃቱ አላቸው ብለን ተስፋ እናደርጋለን። እነዚያ ብረቶች ከተማሪ ቤት ሲመለስ የነበረውን ነብዩን ደብደበው የገደሉ መሆናቸውን እንደሚያስታውሱም እናምናለን። ነብዩ ከመሞቱ በፊት ያን ጨካኝ የህወሃት ነፍሰ ገዳይ እባክህ አትግደለኝ እያለ ሲማፀን፤ ሲያለቅስ ሲያነባ በዓይነ ሂሊናቸው ማየት ይችላሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። እነዚያ ብረቶች የንፁሃንን ደም በከንቱ አፍሠሰዋል። እነዚያ ብረቶች በጋምቤላ፤ በዖጋዴን፤ በአማራ፤ በኦሮሚያ ያፋሰሷቸው ደሞች እንደ አቤል ደም ከምድር ወደ ሰማይ እየጮኹ ነው።ያንን ጩኸት ለመስማት ደግሞ እንደ በረከት ስምዖን ራሳቸውን ይክዳሉ የሚል እምነት የለንም።

አሁን በኢትዮጵያችን ውስጥ ያለው እውነት ይሄው ነው። አርቲስቶቹ የጥበብ ሰው ነን ካሉ፤ ህዝቡ ፊት ለመቆም የሞራል ብቃት አለን ካሉ ከዚህ እውነት ጋር መጋፈጥ ይጠበቅባቸዋል። ስራቸው እንደ መልካም መዓዛ በህዝቡ ዘንድ እንዲወደድ ከፈለጉ በአገሪቷ ውስጥ ያለውን ኢፍታህዊነት፤ ዘረኝነት፤ አድልዎ፤ ጭቆና፤ እንዲሁም የህዝቡን ሮሮ ወደ አደባባይ ማውጣት ይኖርባቸዋል። እውነቱን እምቢ ብለው ከጨካኞቹና ከዘረኞቹ ህውሃቶች ጋር መቆምን ከመረጡ ግን ምርጫቸው ሁል ግዜ እንዳሳፈራቸው ይኖራል እንጂ የሚያስከብራቸው አይሆንም።

በመጨረሻም እናንተ አርቲስቶእች አድምጡን ገንዘባችሁ ህዝብ እንጂ ህወሃት አይደለም። ብትዘፍኑ የሚያዳምጣችሁ፤ ብትቀልዱ የሚስቅላችሁ፤ ብትጽፉ የሚያነብላችሁ ህዝብ እንጂ ዘረኛው ህወሃት አይደለም። ህወሃት የህዝብ ጠላት መሆንን የመረጠ የወሮበላዎች ስብሰብ ነው። ከህወሃት ጎን መቆም በክፋዎች መንገድ መሄድን መምረጥ ነውና አያስመሰግንም።ኢትዮጵያችን ውስጥ በዘረኞቹ ህወሃቶች የሚፈፀመውን ወንጀል ደግፋችሁ ከእነርሱ ጎን መቆምን ከመረጣችሁ ግን ፊሬ አልባዋን በለስ መሆንን መርጣችኋልና ያሳፍራል።

እዚህ ላይም ጥላሁን ገሰሰ “ሃብቴ ህዝቤ፤ ሃብቴ አገሬ” ያለውን አስታውሱ። በእኛ በኩል አበቃን።

ድል ፍትህንና እውነትን ለሚፈልጉ ሁሉ ይሁን !!!

## በጭፍን የወያኔ ደጋፊነት በመሰለፍ በህዝብ ልጆች ላይ ለሚፈጸሙ ጥቃቶች ተባባሪ የሆኑ ወገኖች

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎችን የጥቃቱ ኢላማ አድርጎ በትጋት እየሰራ ነው በማለት አብራርቷል።

ባለፉት አስር ዓመታት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በሀረማያ ዩኒቨርስቲ፣በቴፒ ሚዛን ዩኒቨርስቲና በሌሎችም ተቋማት በሚማሩ የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች ላይ ሆን ተብለው የታቀዱ ስነ-ልቦናዊና ብሄራዊ ጥቃቶች ተሰንዝረዋል። ባለፈው ታህሳስ ወር አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሚማሩ የኦሮሞ ብሄር ተወላጅ ተማሪዎች ላይ የተሰነዘረው ጥቃትም የዚሁ የተቀነባበር ጥቃት ቅጥያ ነው - እንደ መግለጫው።

ይህ ደግሞ የወያኔ መንግስት በማንኛውም ሰዓት የህዝብ ዓመጽ ሊቀሰቀስብኝ ይችላል በሚል ስጋት በተማሪዎቹ ዘንድ ያለውን የአብሮነት ስሜት በመሸርሸር ከፋፍሎ የመምቻ ስልቱ ነው ፤ይሁንና ይህ የወያኔ የቀቢጸ ተስፋ ምኞት ከቶ ሊሳካ አይችልም።ኦሮሞን ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ጋር ለማጋጨት የሚደረገው ጥረትም አይሰምርም ሲል ድርጅቱ በመግለጫው አስረድቷል።

..............................................................................................................................

## የወያኔ እያየለ የመጣዉን የሙስሊም ህብረተሰብ እንቅስቃሴ መቆጣጠር እንዳቃተዉ አንዳንድ የአገዛዙ አባላት ማመናቸዉ ተነገረ

ከአንድ አመት በላይ የተካሄደዉንና ከቀን ወደ ቀን እያየለ የመጣዉን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የመብትና የነጻነት እንቅስቃሴ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ መቆጣጠር ተስኖት ጭራሽ በእንቅስቃሴዉ ጥንካሬና ጽናት እየተደናገጠ መምጣቱን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙት የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች የአገዛዙን ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቅሰዉ በላኩልን ዜና ገለጹ። የኢትዮጵያዉያን እስልምና እምነት ተከታዮችን ትግል አስተባባሪዎች በማሰርና የመጅሊሱን መሪዎች በራሱ መንገድና ቦታ በማስመረጥ ትግሉን የገታ የመሰለዉ የወያኔ አገዛዝ ዛሬ ሁኔታዎች ተለዋዉጠዉ አገዛዙ እራሱ የሚይዘዉና የሚለቅቀዉ ጠፍቶት ህጻናትን በየመንገዱ ተኩሶ መግደል መጀመሩን ዘጋቢዎቻችን አክለዉ ከላኩልን ዜና ለማወቅ ተችላል።

ወያኔ በአንድ በኩል ተሳትፎዉ እያደገ በመጣዉ የሙስሊሞች እንቅስቃሴ ተደናግጦ ግራ የተጋባ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሙስሊሙ ህብረተሰብ በመጪዉ የወረዳና የአካባቢ ምርጫ አይሳተፍም በሚል "ምን እናድርግ" የሚል ከፍተኛ ስጋት ዉስጥ መግባቱን ለማወቅ ተችሏል። በአሁኑ ወቅት ወያኔን በከፍተኛ ደረጃ ያሳሰበዉ የሙስሊሙ ህብረተሰብ በሚመጣዉ የወረዳና የአካባቢ ምርጫ አለመሳተፉ ብቻ ሳይሆን እያየለ የመጣዉ እንቅስቃሴ ምርጫዉን ማስተጓጎል መቻሉና ብሎም እቅስቃሴዉ በዚህ ከቀጠለ የአገዛዙ የሃያ አንድ አመት የስልጣን ዘመን ማጠር እንደሚችል ወያኔ ከወዲሁ መገንዘብ በመቻሉ ጭምር ነዉ። ስለሆነም ወያኔ የሙስሊሙ ህብረተሰብ እንቅስቃሴ በምርጫዉ ላይ ሊኖረዉ የሚችለዉን ተጽዕኖ ለመገደብ በሚል ያለ የሌለ ካድሬዎቹን፤ መሪዎቹንና "የእንድ ለአምስት" አባላቱን ቤት ለቤት እየዞሩ ሙስሊሙንና ሌላዉንም የህብረተሰብ ክፍል ለምርጫዉ እንዲመዘገብ ማስጨነቅ ጀምሯል።

የወያኔዎች ጭንቀት ህዝቡ ይመርጠኛል ወይም አይመርጠኝም ሳይሆን የእነሱ ጭንቀት ምርጫዉን ህዝብ የተሳተፈበት ምርጫ ለማስመሰል ነዉ እንጂ ወያኔ ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ምርጫ ኖረ አልኖረ ህዝብም መረጠ አልመረጠ አሸናፊዉ ሁሌም ወያኔ ብቻ ነዉ ሲሉ አንድ ሰማቸዉ እንዳይጠቀስ የጠየቁን የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁር ተናገሩ። ምሁሩ ንግግራቸዉን በመቀጠል እንደ ሰደድ እሳት በመቀጣጠል ላይ ያለዉን የሙስሊም ህብረተሰብ እንቅስቃሴ ለማብረድ ወያኔ ማድረግ ያለበት የተጠየቀዉን ጥያቄ መመለስ ነዉ እንጂ ጠያቂዎቹን መግደል አይደለም ብለዋል። እኚሁ በወያኔ መጠን የለሽ ጭካኔ የተማረሩት ምሁር ጥያቄያችን ህጋዊ ተቃዉሟችንም ህጋዊ ነዉ ፤ ወያኔ በየመንገዱና በየአደባባዩ የሚደበድባቸዉና የሚገድላቸዉ ዜጎቻችን ደም የመብታችንንና የነጻነታችንን መከበር ያፋጥነዋል እንጂ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ለወያኔ የፈሪ በትር በፍጹም አይንበረከክም ብለዋል።

ይህ በንዲህ እንዳለ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተከስቶ የነበረውን የብሄር ግጭት ተከትሎ ከ100 በላይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መታሰራቸውን የአፍሪካ ቀንድ የሰብአዊ መብት ሊግ ባወጣው መግለጫ አስታውቋል። ታስረዋል ያላቸውን የ99 ተማሪዎች ስም ዝርዝር ይፋ ያደረገው የሰብአዊ መብት ድርጅቱ አብዛኞቹ ከቀላል እስከ ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ጠቁሟል። ከታሰሩት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የኦሮሞ ተወላጆች ቢሆንም፣ የአማራና የትግራይ ተማሪዎችም ይገኙበታል።

## ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የመለስ ወንበር ወይም የመለስ ጓደኞች አልተስማሙትም ሲሉ አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን አሾፉ

አንደ ፈረንጆቹ የዘመን አቆጣጠር መስከረም 21 ቀን 2012 ዓም ቃለ መሃላ ፈጽሞ በኢትዮጵያ ታሪክ ለሁለተኛ ግዜ በጠ/ሚኒስትርነት ደረጃ የመንግስት መሪ ለመሆን የበቃዉ ሀ/ማሪያም ደሳለኝ አገርን የመምራት ሀላፊነት፤ የህወሀት ባለስልጣኖች ጫናና ከቀን ወደ ቀን እየባሰበት የሄደዉ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ከግቡ አደርሳለሁ ብሎ ከሚታገልለት "የመለስ ዜናዊ ራዕይ" ጋር እየተጋጨበት በየቀኑ ከራሱ ጋር እየተጣላ እንደሚዉል የግንቦት ሰባት ዘጋቢዎች አንድ የአገዛዙን ከፍተኛ ባለስልጣን ጠቅሰዉ ዘገቡ። እኚህ ስማቸዉ እንዳይጠቀስና ድምጻቸዉም በሬዲዮም ሆነ በቴሌቪዥን እንዳይሰማ አደራ ያሉን የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣን ሀ/ማሪያም ደሳለኝ ስልጣን ከያዘበት ቀን ጀምሮ የሚቀመጥበት የመለስ ወንበርም ሆነ አለቆቹ የሆኑት የመለስ ዜናዊ ጓደኞች አልተስማሙትም ሲሉ በ47 አመቱ የአገሪቱ ጠ/ሚኒስትር ላይ አሹፈዋል።

ገና ስልጣን ከመያዙ ስራዬ የመለስን ረዕይ ከግቡ ማድረስ ነዉ ብሎ ለአገሩና ለህገ መንግስቱ ሳይሆን ለቀድሞ ጌታዉ ታማኝነቱን የገለጸዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ እንኳን በህዝብ የተጠላዉን የመለስን ራዕይ ከግቡ ማድረስ የቀን ከቀን የአገር መሪነት ስራዉን በነጻነት ማከናወን አለመቻሉን ብዙዎች በአጽንኦት በመናገር ላይ ናቸዉ። በተለይ በቅርቡ የህወሀት አባት በመባል የሚታወቀዉ ስብሀት ነጋ "የመለስ ራዕይ" የሚባል ነገር የለም ያለዉ ራዕይ የሁላችንም ራዕይ ነዉ ብሎ ከተናገረ በኋላ ዬኔ ነዉ የሚለዉ የራሱ ራዕይ የሌለዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ኮምፓሱ እንደተበላሸ አዉሮፕላን ማረፊያዉ ጠፍቶት ከጎራ ጎራ እየዋለለ መሆኑን ከገዢዉ ፓርቲ ከኢህአዴግ አካባቢ እየሾለኩ የሚወጡ ዜናዎች ያስረዳሉ።በተለይ አገሪቷንም ሆነ የወያኔን አገዛዝ ከወዲህ ወዲያ በማንገዳገድ ላይ የሚገኘዉ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ ለኃ/ማሪያም ደሳለኝ ትልቅ እራስ ምታት ሆኖ መሰንበቱ በግልጽ የታየ ሀቅ ሆኗል። ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የሙስሊሙን ህብረተሰብ ጥያቄ ለመፍታት አቅሙም ፋላጎቱም አለዉ ብለዉ ብዙዎች የሚያምኑ ቢሆንም በህወሀት አለቆቹ የሚታዘዘዉ ኃ/ማሪያም ግን እስካሁን ድረስ አለቆቹ የሚሰጡትን ትዕዛዝ ከማስፈጸም ዉጭ ችግሩን ለመፍታት የወሰደዉ ምንም እርምጃ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል።

## በወያኔ ሰራዊት መካከል ቡሬ ግምባር ላይ ተፈጥሮ የነበረው የእርስ በርስ ውጊያ ... (ከገጽ 3 የዞረ)

በለሌ በኩል ደግሞ ወያነ "ሽብርተኞችን " ትረዳላችሁ ወይም "ከሽብርተኞች " ጋር ትገናኛላችሁ በሚል በቡሬና በሌሎችም የአገሪቱ የጠረፍ አካባቢዎች የሰፈሩ ወታደሮችን ትጥቅ እያስፈታ ማሰር መጀመሩን ለዝግጅት ክፍላችን በተከታታይ የሚደርሱ መረጃዎች ያመለክታሉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ እንደ ሰደድ እሳት በመቀጣጠል ላይ ያለዉ ጸረ ወያኔ እንቅስቃሴ ያስደነገጠዉ ወያኔ የነጻነት ህይሎችን ይቀላቀላሉ ብሎ የጠረጠራቸዉን ወታደሮቸ በየቀኑ እስር ቤት እየወረወረ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል።ይህንን በተመለከተ ከፍተኛ ወታደራዊ ችሎታና ልምድ ያላቸዉ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር አባላትና በመከላከያ ኢንጂነሪንግ የሰለጠኑ ወጣት መኮንኖች ከየቦታዉ በስምና በዘር እየተመረጡ በመታሰር ላይ ናቸዉ። ባጠቃላይ ወያነ በአሁኑ ወቅት ከትግርኛ ተናጋሪዎች ውጭ በሌሎች የሰራዊቱ አባላት ላይ ምንም አይነት እምነት እንደለለዉ በሚወስዳቸዉ እርምጃዎች ያሳየ ሲሆን ይህንን የተረዱ የመከላከያ ሰራዊት አባላት አጋጣሚውን ባገኙ ግዜ ሁሉ የታጠቁትን መሳሪያ እንደያዙ የነጻነት ሀይሎችን በመቀላቀል ላይ መሆናቸዉን ከየቦታዉ የሚደረሱን ዘናዎቸ ያስረዳሉ።

ለየት ባለና በዛረዉ ቀን በደረሰን ዜና መሰረት ዘረኛዉ የወያነ አገዛዝ የ "ነኢሰን" ወይም በሙሉ ቃሉ የነጻ ኢትዮጵያ ሰራዊተ ንቅናቀ አባላት ናችሁ የሚላቸዉን የመከላከያ ሰራዊት አባላት ከየጦሩ ሰፈር እየሰበሰበ በማሰር ላይ መሆኑን የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ወታደራዊ ምንጮቸን ጠቅሰዉ በላኩልን ዘና ገለጹ። ነኢሰን የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ከህወሀት መሳሪያነት ተላቅቆ የአገርና የወገን አለኝታ እንዲሆን የሚታገልና ኢትዮጵያ ሰራዊት ዉስጥ የበቀለ ንቅናቀ ነው። ነጻ ወይም ነጻነት የሚለው ቃል ከራሱ ስም ዉጭ ሌላ የትም ቦታ እንዲሰማ የማይፈልገው ህወሀት ግን ነኢሰንን ገና ከመፈጠሩ ማጥፋት አለብኝ በሚል

| | |
|---|---|
| ሻ/ቃ ቃለአብ ከበደ | ሻ/ቃ ኪሲ ጎበሹ |
| ሻ/ቃ ሰለሞን አለሙ | ሻ/ቃ ሞገስ መለሰ |
| ሻ/ቃ ታቦር ኢዶሳ | ኮሎነል ሙሉገታና ሻለቃ አስረስ |
| ሻ/ቃ ተረፈ ማሞ | |

የሚባሉ ስምንት የአማራና የኦሮሞ ስም ያላቸዉን ከፍተኛ መኮንኖች ከያሉበት ሰብስቦ የረጂም ግዝ አገልግሎታቸውን በመሰረዝ ያለጡረታ ከሰራዊቱ እንዲባረሩ አደርጎአል።

## ወያኔ የሰዉ መግደል ወንጀል ሙያዉን ይዞ አሜሪካ መጣ- ጋዜጠኛ አበበ ገላዉን ... (ከገጽ 1 የዞረ)

በሂደት ላይ በመሆኑ ዝርዝር መረጃ ከመስጠት ቢቆጠቡም፣ ኤፍ ቢ አይ እንደዚህ አይነት ወንጀሎችን በቸልታ እንደማይመለከት ገልጸው የውጭ አገር ሰላዮችም ሆኑ ተወካዮች አሜሪካ ዉስጥ የማንንም ዜጋ ሰብአዊ መብት በሚደፍር ህገወጥ ወንጀልና በማስፈራራት ስራ ተሰማርተዉ ሲገኙ ኢትዮጵያዊያን በቸልታ ማለፍ እንደማይገባቸው አሳስበዉ እንደዚህ አይነት ጻረ ህዝብና ጻረ አገር እንቅስቃሴዎችን በአካባቢያቸው ለሚገኙ የኤፍ ቢ አይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጥቆማ እንዲያደርጉ አደራ ብለዋል።

ጋዜጠኛ አበበ ገላዉን ለመግደል የተደረገዉን ሙከራ አስመልክቶ ዋሺንግተን ዲሲ የሚገኘዉ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ ያናገራቸዉ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና ታዋቂ ግለሰቦች ይህ ወያኔ አሜሪካ ድረስ ይዞት የመጣዉ የግድያ ሴራ እንዳልገረማቸዉ ተናግረዋል። የግንቦት ሰባት የፍትህ፤የነጻነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነት ዘርፍ ሀላፊ የሆኑት አቶ ኤፍሬም ማዴቦ ወያኔ አገር ቤትም ሆነ ዉጭ አገር አንድ የተካነበት ስራ ቢኖር የሚቃወሙትን ሰዎች መግደል ነዉና የወያኔ ግድያ ቤታችንን ከማንኳኳቱ በፊት ይህን ነብሰ ገዳይ ቡድን ከአገራችን ነቃቅለን ከማጥፋት ሌላ አማራጭ የለንም ሲሉ አንድ ፏሪነታቸዉ ሜሪላንድ ግዛት ዉስጥ የሆነ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ደግሞ አገራችን እስከዛሬ የምትታወቀዉ በቡና ላኪነት ነበር አሁን በወያኔ ዘመን ግን ሰላይና ነብሰ ገዳዮች መላክ ጀመረች በማለት ጥያቄያችንን ቁም ነገር ባጀበዉ ቀልድ መልሰዋል።

የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

__መካከኛ ሞገድ__:- በ 358 MB, በ 837 kHz
__አጭር ሞገድ__:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

__ማሳሰቢያ__:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org